# 121ኛውን የአድዋ በዓል በጨረፍታ…

**ስለሞን ሽፈራው 03-07-17**

እውን ታሪክ በሰው ልጆች  ህይወት ውስጥ ተጨባጭ ጠቀሜታን ሊሰጥ የሚችል ነገር ነውን? ከሆነስ  ጠቀሜታው እንዴት ይገለፃል? የሚል ጥያቄ የሚያነሱ ወገኖች መኖራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ እናም ይህን የመከራከሪያ ነጥብ ግልፅ በማድረግ ረገድ የዘርፉ  ሊቃን የየራሳቸውን ማብራሪያ ለመስጠት ሲመክሩ መስማት የተለመደ ጉዳይ ነው ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም፡፡ ከዚህ አኳያ የሀገራችን የታሪክ ትምህርት ሊቃውንትም ጭምር ሙያዊ ትንተናዎችን ሲሰጡ የሚደመጥበትን አግባብ እንደ አብነት ማቅረብ እንደሚቻልም ነው የሚሰማኝ፡፡

እንግዲያውስ እኔም ለዚህ አጭር መጣጥፌ መንደርደሪያ እንዲሆነኝ የማደርገው ከአንጋፋ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል ፕሮፌሰሮቻችን አንዱ የሆኑት ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ ከላይ ለተነሳው ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ ነው፡፡ ስለዚህም ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ፤በ2008 ዓ/ም መጨረሻ ላይ ታትሞ ለወጣው የአዲስ አድማስ ጋዜጣ እትም ከሰጡት ቃለምልልስ ውስጥ፤ በተለይም ለዚህ ፅሁፍ ማጠንጠኛ ርዕሰጉዳይ አስፈላጊ ሆኖ ያገኘሁትን ነጥብ ቀንጭቤ እጠቅሳለሁ፡፡

‹‹…ይኼ እንኳን ታሪክን መማር ለምን አስፈለገን ብሎ እንደመጠየቅ ነው›› ሲሉ የአዲስ አድማሱ ጋዜጠኛ ዓለማየሁ አንበሴ ላቀረበላቸው ጥያቄ ምላሻቸውን መስጠት የጀመሩት ፕሮፌሰሩ ‹‹ለማንኛውም ግን ታሪክን መማር ወይም ማወቅ የሚያስገኝልን ዋነኛ ጥቅሞችን ብንናገር ነው የሚሻለው›› በማለት ቀጠሉና የሚከተሉትን ነጥቦች አስቀመጡ…፡፡

‹‹እንደ ዋነኛ ታሪክን የመማር ጠቀሜታ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው መሰረታዊ ነጥብ እኛ ኢትዮጵያውያን ህዝቦች ከየት ተነስተን ነው አሁን ወደምንገኝነበት የሀገራችን አጠቃላይ ሁኔታ ለመድረስ የቻልነው? የሚለውን ጥያቄ በሚመለከት ታሪካዊ መዛግብትን መሰረት ያደረገ መረጃ እንዲኖረንና አዲሱ ትውልድ ስለትክክለኛ ማንነቱ የተሟላ ዕውቀት እንዲቀስም በማድረግ ረገድ ያለው ገንቢ አስተዋፅኦ ነው ማለት ይቻላል›› ሲሉ የጉዳዩን ፍሬ ሃሳብ የሚያስገነዝብ ማብራሪያቸውን ለጋዜጠኛው የሰጡት ፕሮፌሰሩ፤በተለይም ከታሪክ ሂደት ስለመማር አስፈላጊነት ለማስረዳት የሞከሩበት ገለፃ የጋራ ችግሮቻችንን ለመፍታት ሲባል ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተሰምቶኛል፡፡

ይህን ያልኩበት ምክንያት ‹‹ሌላው ታሪክን ከመማርና ከማወቅ ሊገኝ የሚችለው ጠቃሚ ቁምነገር ደግሞ በተለይም ሀገር የሚመሩት ፖለቲከኛች፣ያለፉት መንግስታት የፈፀሙትን ታሪካዊ ስህተት ላለመድገም እንዲጠነቀቁና እንዲሁም የትናንቱ ትውልድ ከሰራቸው መልካም ተግባራት ላይ የዛሬው ትውልድ የራሱን ጥረት እንዲያክልባቸው ለማድረግ የሚያበረክተው በጎ አስተዋፅኦ ነው›› ሲሉ አክለው የሰነዘሩትን የፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ ሃሳብ ወድጄዋለሁና ነው፡፡ ስለሆነም፣ ከዚሁ አንጋፋዎቹ የታሪክ ትምህርት ክፍል ሊቃን ዜጎቻችን ከሚሰጡት ምክር አዘል አስተያየት በመነሳት፣ ለመሆኑ ዘንድሮ ለ121ኛ ጊዜ የተከበረውን የዓድዋ ድል በዓል ታሪካዊ ገፅታስ ከላይ ለአብነት ያህል በተጠቀሰው የፕሮፌሰሩ ሙያዊ ትንተና ውስጥ የተመለከቱትን ሀገርአቀፋዊ ፋይዳዎች እንዲያስገኝልን ማድረግ በሚያስችል መልኩ ቃኝተነዋል ወይ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ስለመሰለኝ ነው እኔ ዛሬ እቺን ፅሁፍ ለመጫጫር የተገፋፋሁት፡፡

መቼስ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንደ አንድ ህብረተሰብ የምንጋራው ሀገር አቀፋዊ የጋራ ርዕሰ ጉዳይ እንዲኖረን በማድረግ ረገድ ቀዳሚ ስፍራ ሊይዝ የሚችለው በተለይ ጀግኖች አያቶቻችን ዓድዋ ላይ ከጣያን ወራሪ ሰራዊት ጋር ገጥመው መላውን የምዕራቡ ዓለም ቅኝ ገዢዎች ያሳፈሩበት አንፀባራቂ የድል አድራጊነት ታሪካችን ነው ብሎ መደምደም ተገቢ ይሆናል፡፡ ይልቁንም ደግሞ መላው የሀገራችን ህዝቦች፣ ፊርጀብዙ መስዋዕትነትን በጠየቀ የዘመናት ትግላቸው አማካኝነት የተቀዳጁቸውን ሕገ መንግስታዊ መብቶች ሁሉ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ ማድረጋችንን ቀጥለን፣ እንደ ህብረተሰብ አንገታችንን ደፍተን በዓለም ታሪክ ፊት ምፅዋት ስንጠይቅ ከምንታወስበት አሳፋሪ የድህነትና የኋላ ቀርነት ታሪካችን ሙሉ በሙሉ ለመላቀቅ የሚያስችለንን ሀገራዊ የጋራ መግባባት ይበልጥ በማጠናከር ረገድ የአድዋ ድል አንፀባራቂ ታሪካችን፣ዓይነተኛ የአሸናፊነት ተምሳሌት ሆኖ የማያገለግልበት ምክንያት እንደማይኖር ነው በርካታ አስተያየት ሰጭዎች የሚስማሙበት፡፡

ስለዚህም፣ ባለፈው ሐሙስ የካቲት 23 ቀን 2009ዓ.ም 121ኛ ዓመቱን ያከበርንለት የአድዋው የድል ገድል ውሎ ከሚነገርለት በላይ ግዝፈት ሊጎናፀፍ እንደሚገባና በዚያው ልክም ለዛሬዋ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዘለቄታዊ የጋራ ዕጣ ፈንታ መቃናት የሚበጅ ተጨባጭ ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ እንደሚጠበቅብን ነው እኔ ላሰምርበት የምሻው፡፡ ለዚህ አገር አቀፋዊ የቤት ስራችን መሳካት እከሌ ከእከሌ ሳይባል፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወገን የየድርሻውን መወጣት እንደሚጠበቅበትም የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም፡፡ በተለይም

ደግሞ የኢፌደሪ መንግስትና እንዲሁም የሁሉም ክልላዊ መስተዳድሮች የአመራር አካላት፣ ታላቁ የዓድዋ ድል ገድል ከኛም አልፎ መላውን የአለም ጥቁር ህዝቦች የሚያስመካ የኩራት ምንጭ ተደርጎ የሚቆጠርበትን አንፀባራቂ ታሪክ ለወጣቱ ትውልድ በቅጡ የማስረዳት ኃላፊነት እንዳለባቸው መዘንጋት አይኖርበትም፡፡

ስለሆነም፣ ይህ ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከተው የባህል እና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ በዘንድሮው የዓድዋ ድል በዓል አከባበር ላይ ያሳየውን መነቃቃት ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ሊገፋበት እንደሚገባና ክብርት ሚኒስቴሯ ዶክተር ሒሩት ወ/ማሪያም ዘመን አይሽሬውን አንጸባራቂ የድል ታሪክ በተሰራበት ዓድዋ ከተማ ተገኝተው በዓሉን ላከበረው ህዝብ ባሰሙት ንግግር ያቀረቡትን ወቅታዊ ጥሪ ሁሉም ወገን በቅንነት መንፈስ ሊቀበለው እንደሚገባ ይሰማኛል፡፡ በዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ዘመነ  ጀግኖች ኢትዮጵያውያን አያቶቻችን  ለጋራ ነፃነታቸው መከበር ሲሉ የአውሮፓን ቅኝ ገዢዎችን ገጥመው ያንበረከኩበት የዓድዋ ድል ወርቃማ ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ የሚገባውን ያህል ተገቢ ስፍራ ሳይሰጠው ለመቆየቱ እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ነጥብ፣ ሀገራችንን ለተመፅዋችነት ዳርጓት የቆየው ድህነትና ኋላቀርነታችን ነው ተብሎ ይታመናል፡፡  ይህ የአሁኑ  ትውልድ ለታላቁ የዓድዋ ድል ታሪካችን ድምቀት መደብዘዝ ምክንያት ሆኖ ከቆየው ፈርጀ ብዙ ድህነትና ኋላቀርነት ጋር የሞት ሽረት ትግል ገጥሞ በሚገኝበት ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ሆነን ያከበርነውን የዘንድሮው የዓድዋ ድል በአል በጨረፍታ የተመለከትኩበትን መጣጥፌን ከማጠቃለሌ በፊት ማስታወስ የሚኖርብኝ ጥቂት ጠቃሚ ነጥቦች አሉ፡፡

እናም ሐሙስ የካቲት 23 ቀን 2009ዓ.ም 121ኛውን የአድዋ ድል በአል ለማክበር፣ አንፀባራቂው የድል ታሪካችን ወደተሰራበት ስፍራ ካመሩት የኢፌዴሪ መንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች አንደበት የተደመጡ ንግግሮችን እዚህ ላይ አንስቼ በመጥቀስ ነው ሃሳቤን ማጠቃለል የሚኖርብኝ፡፡ ስለዚህም ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን አያቶቻችን፣ ከዛሬ 121 ዓመት በፊት የማይሞከር ጉዳይ ይመስል የነበረውን ዓለም አቀፍ አስተሳሰብ ለመለወጥ ያስቻለ ታሪክ ሰርተው በአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ላይ የተቀዳጁትን አንፀባራቂ ድል መላውን አፍሪካውያን ህዝቦች ወደ ነፃነት እንዲያመሩ  በማድረግ ፈር እንደቀደደ ሁሉ፣ የአሁኑ ኢትዮጵያዊ ትውልድ፣ በአባይ ጉባ  እየተሰራ ያለው የፀረ ድህነት ታሪክም ሀገሪቱን ወደ ሌላ አዲስ ምዕራፍ የሚወስድ የብልፅግና ገድል ተደርጎ እንደሚቆጠር በበዓሉ አከባበር ስርዓት ላይ የተገለፀበት አግባብ ምን ይመስል እንደነበር ለአብነት ያህል እንመልከት፡፡

ዘንድሮ ለ121ኛ ጊዜ የተከበረውን የአድዋ ድል በአል ለማክበር አንፀባራቂው ታሪካችን በተሰራበት ስፍራ የተገኙት የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ ‹‹…መላው የአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከአራቱም ማዕዘናት ክተት ተጠራርተው በመዝመት ፤ የዛሬ 121 ዓመት እዚህ ታሪካዊ ቦታ በወራሪው የጣሊያን ቅኝ ገዥ ሰራዊት ላይ የተቀዳጁትን አንፀባራቂ ድል ስናስብ፤የያኔዎቹ ወላጆቻችንም ጭምር በአንዲት ነፃነቷ በተጠበቀ ልዑላዊት ሀገር ጣራ ስር አብሮ መኖር ይቻላል የሚል እምነት እንደነበራቸው እንረዳለን›› ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ የአሁኑ ትውልድም የዓድዋ ድል ጀግኖች አያቶቹ በከፈሉት ፈርጀ ብዙ መስዋዕትነት ላይ የተጣለውን የኢትዮጵያዊነት ፅኑ መሰረት የሚፈታተኑ አፍራሽ ተግባራት ታቅቦ፤ ለመላው የሀገራችን ህዝቦች በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ይበልጥ መጠናከር የሚበጀውን አስተሳሰብ ሊያዳብር እንደሚገባም ነው ክቡር ፕሬዘዳንቱ በንግግራቸው ማጠቃለያ ያሰመሩበት፡፡

እንዲሁም ደግሞ ሌላው በዘንድሮ የዓድዋ ድል በአል ላይ ለመገኘት ወደ ትግራይ አቅንተው የነበሩት የኢፌዴሪ መንግስት ከፍተኛ የስራ ኃላፊ፤ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቶ ደመቀ መኮንን ‹‹ከዛሬ 121 ዓመት በፊት ነሎች በመላው ጥቁር ህዝቦች ጫንቃ ላይ ጭነውት የነበረውን የቅኝ ግዛት ቀንበር እንዲሰባበርና እንዲቀበር ያደረገ አርአያነት ያለው የዓድዋ ድል አንፀባራቂ ታሪካችን፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ብሔሮች፤ብሔረሰቦችና ህዝቦች በጋራ ጠላታችን ላይ ተባብረን ከተነሳን የማናሸንፈው ምድራዊ ሃይል ሊኖር እንደማይችል የሚያረጋግጥ ተግባር ነው ማለት ይቻላል›› ሲሉ ነው የተናገሩት፡፡

‹‹እነሆ የአሁኑ ትውልድም ጀግኖች ኢትዮጵያውያን አያቶቻችን ክንዳቸውን አስተባብረው በመነሳት ቅኝ ግዛትን ድባቅ የመቱበትን የዓድዋን የድል ታሪክ በድህነት ላይ ለመድገም ቆርጠው ተነስተዋል ›› ሲሉ ያከሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤የፀረ ድህነት ትግሉ ዓይነተኛ መገለጫ፤ (በእርሳቸው አባባል ‹‹የስበት ማዕከል››) ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ግድብ እንደሆነም ነው ያሰመሩበት፡፡ ስለዚህም እንደኔ እምነት ከሆነ ለዘንድሮ የአድዋ ድል በአል ድምቀት የሰጠነውን ትኩረት ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ልንቀጥልበት ያገባል ባይ ነኝ፡፡ ያን ማድረግ ስንችል ደግሞ፤የኢትዮጵያን የህዳሴ ጉዞ በማፋጠን ረገድ ሁሉም የሀገራችን ህዝቦች የሚጠበቅባቸውን ያህል ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ የሚጋብዝ የጋራ መድረክ እንፈጥራለን እንጂ፤ የትኛውንም ወገን የሚያከስር ነገር አይኖረውምና ጉዳዩ ተገቢ ትኩረት ይሰጠው እላለሁ እኔ እንደ አንድ ዜጋ፡፡